## ቅጽ 9. ነፃ የማህበረሰብ አገልግሎት ስለማበርከት ማረጋገጫ

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት

[ወይም]

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሱፔሪየር ፍርድ ቤት

| | | |
|---|---|---|
| ______________________________ ከሳሽ/ይግባኝ ጠያቂ | ) ) ) | **ነፃ የማህበረሰብ አገልግሎት ስለማበርከት ማረጋገጫ** |
| v. | ) ) ) | |
| ______________________________ ተከላካይ/የይግባኝ ተጠያቂ | ) ) ) | የጉዳዩ ቁጥር: ______________________ |
| ______________________________ | ) ) | |

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ደንብ ቁጥር 49(c)(8) and 49(c)(9) መሰረት የሚከተለውን አረጋግጣለሁ፡-

1. እኔ በሚከተሉት የጥብቅና ሙያተኞች ማህበር/ራት ግዴታዬን ሁሉ አሟልቼ የምገኝ አባል መሆኔን፡-

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

2. ☐ በስነምግባር ጉድለት ምክንያት በየትኛውም አስተዳደር ወይም ፍርድ ቤት በሙያዬ እንዳላገለግል እገዳ አልተደረገብኝም ወይም ማእቀብ አልተጣለብኝም ከዚሁም ጋር በየትኛውም አስተዳደር ወይም ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶብኝ በእንፐልፐል ባለ ጉዳይ ምክንያት በገዛ ፍቃዴ ከጠበቆች ማህበር አባልነቴ አልለቀቅኩም።

3. ከሚከተሉት አንዱን ይምረጡ፡-

   ☐ (ሀ) በደንበ ቁጥር 49 (c)(9)(A) መሰረት እኔ የዲሲ ባር በመባል በሚታወቀው የጠበቆች ማህበር ተመዝገቤ በሙያዬ በንቃት የማገለግል፤ ከዚሁም ጋር እኔ የህግ አገልግሎት በሚያበረክት ድርጅት ውስጥ ተቀጥሬ የማገለግል ወይም ጠበቆችን በሚጠቁም ፕሮግራም ውስጥ ተሳታፊ ነኝ። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት ጥብቅና የቆምኩት ያለ ምንም ክፍያ በነፃ ነው። ወይም

   (ለ) በደንብ ቁጥር 49 (c)(9)(B) መሰረት እኔ በህግ ፊት ራሳቸውን ለመከላከል የገንዘብ አቅም ለሌላቸው በመቆም በሚታወቀው ፐብሊክ ዲፌንደር አገልግልግሎት ከሚባል ድርጅት ጋር ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሚገኝ ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ የማያስከፍል ወይም ለስሙ ያህል ለስራ ማካሄጃ ዝቅተኛ ክፍያ የሚያስከፍል ለትርፍ ያልቆመ ድርጅት የምሰራ ነኝ። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በህግ ስራ ሙያ ለመሰማራት ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ባር አሶሲየሽን ማመልከቻ ያቀረብኩ ወይም በዲስትሪክተ ኦፍ ኮሎምቢያ በህግ ሙያ መስራት በጀመርኩ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ማመልከቻዬን የማስገባ ሲሆን እኔን የሚቆጣጠረኝ ግለሰብ ለፐብሊክ ዲፌንደር አገልግሎት ወይም ለትርፍ ያልቆም ድርጅት የሚያገለግል በዲሲ ባር ተመዘግቦ ንቁ ተሳትፎ በሚያደርግ

☐ አባል ሲሆን የዚህ ግለሰብ ፊርማና የባር ቁጥር ከዚህ በታች ቀርቧል። ወይም

(ሐ) በደንብ ቁጥር 9 (c)(9)(C) መሰረት እኔ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት መኮንን ወይም ተቀጣሪ ሰራተኛ ስሆን ይህንን ጉዳይ እንድይዝ የተመደብኩት ወይም የተጠቆምኩት ሕዝቡን ያለ ክፍያ በሚያገለግል ድርጅት ነው። በተጨማሪ እኔን የሚቆጣጠረኝ ግለሰብ በዲሲ ባር ተመዘግቦ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግ አባል ሲሆን የዚህም ግለሰብ ፊርማና የባር ቁጥር ከዚህ በታች ቀርቧል። ወይም

☐ (መ) በደንብ ቁጥር 49 (c)(8) መሰረት እኔ የምሰራው በዲሲ ባር ተመዘግቦ ንቁ ተሳትፎ በሚያደርግ አባል  ቀጥተኛ ተቆጣጣሪነት ሲሆን የዚህም ግለሰብ ፊርማና የባር ቁጥር ከዚህ በታች ቀርቧል። እኔ ለዚህ ጉዳይ በጥብቅና የቆምኩት ያለ ክፍያ ነው። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በህግ ስራ ሙያ ለመሰማራት ለዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ባር አሶሲየሽን ማመልከቻ ያቀረብኩ ወይም በዲስትሪክተ ኦፍ ኮሎምቢያ በህግ ሙያ መስራት በጀመርኩ በዘጠና (90) ቀናት ውስጥ ማመልከቻዬን የማስገባ ይሆናል። በዚህ ግዜአዊ የመስራት ስልጣን ከ360 ቀናት በላይ በህግ ሙያ የማላገለግል ሲሆን የኔን የባር ምዝገባ ውጤትና ቁጥጥር ሁኔታ ለህዝቡ በአግባቡ አሳውቃለሁ።

በደንብ ቁጥር 49 (c)(9) መሰረት ልክ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የጠበቆች ማህበር በአባልነት ተመዝግቦ ተሳትፎ በማድረግ ላይ እንዳለ ጠበቃ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የጥብቅና ሙያተኞች ሙያዊ ስነ ምግባርና ከዚሁ ጋር አብሮ ተያያዥ ሆኑ የአፈፃጸም ሂደቶች ደንብ የምገዛ መሆን እንዳለብኝ ገብቶኛል። በተጨማሪ እኔ በጥብቅና ሙያ የማገለግልባቸው ፍርድ ቤቶች ለሚኖራቸው ስልጣን ተገዥ መሆን እንዳለብኝ ገብቶኛል።

____________________________________________________________

ያረጋገጠው ሰራተኛ ፊርማ ስም ቀን

____________________________________________________________

የስራ ቦታ አድራሻ

____________________________

ስልክ ቁጥር

____________________________________________________________

በደንብ ቁጥር 49(c)(8) and (c)(9) መሰረት
የጥብቅና ሙያተኞች ማህበር አባል ፊርማ የዲሲ ባር ቁጥር ቀን